# ቀስተደመና ሬድዮ ትችት

(26.07.02)

# እድገት ሌላ ልማት ሌላ

በምርት መጨመርና በህዝብ ኑሮ መሻሻል ማለትም በእድገትና በልማት መሃከል ያለው ግንኙነት ለብዙ ጊዜ ሲያከራክር የቆየና ዛሬ ደግሞ በተለይ ባለንበት የግሎባላይዜሽን ወቅት በማገርሸት ላይ ያለ ክርክር ነው። በአንድ ወገን «ዋናው የምርት ማደግ ነው፣ ይህ ከተሳካ የግድ የህዝብ ኑሮ መሻሻልና መደላደል ይከተላል።» የሚሉ ሃይሎች አሉ። በሌላ ወገን የተሰለፉ ሃይሎች ይህንን አካሄድ «እድገት ያለልማት» በሚል አባባል ያጣጥሉታል። ከዚህም አልፈው ይህ አካሄድ አንድን አገር የልማት ሳይሆን የጥፋት ጎዳና ሊያስይዝ የሚችል አደገኛ አካሄድ ብለው ይቃወሙታል።

እድገትና ልማት አንድ እንዳይደሉ፣ በየአመቱ ምርት መጨሩን ለማሳየት የሚደረደሩ ስታቲስቲክሶች የግድ የህዝብ ኑሮ መሻሻልና ሳይሆን እንዲያውም ከበስተጀርባቸው የህዝብ ኑሮ ደረጃ ማሽቆልቆልን ሲያመለክቱ እንደሚችሉ ዛሬ በሃገራችንም ሆነ በአለም አቀፍ ደረጃ ግልጽ እየሆነ የመጣ ክስተት ነው።

በኢትዮጵያችን ደረጃ የምናየው ምንድን ነው? በያዝነው ሳምንት የተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን የኢትዮጵያን እድገት አስመልክቶ ስታቲስቲክስ ይፋ አድርጉዋል። ባጭሩ የሚባለው ምንድን ነው? በያዝነው አመት የሃገራችን ኢኮኖሚ በስድስት በመቶ አድጉዋል። ይህ ማለት የስልሳ አምስት ሚልዮን ኢትዮጵያውያን የእያንዳንዳቸው የአመት ገቢ በስድስት ከመቶ አደገ ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ግልጽ ያልሆንላቸው ሰዎች ካሉ ራሱ ኮሚሽኑ ከዚህ የእድገት አሃዝ ጋር አያይዞ የሚለውን ይመልከቱ። እዛው በዛው ደግሞ በሃገሪቱ ድህነት ከፍቷል፣ በሃገሪቱ ስራ አጥነት ጨምሯል ይለናል። በአጭሩ እድገት አስመዝግበናል። ለህዝባችን ግን ልማት አላገኘንም።

በአለም አቀፍ ደረጃም ቢሆን የሚታየው ይኸው ነው። ከአስር አመታት ወዲህ በአለም ደረጃ እየተንሰራፋ የሄደው ግፈኛ የግሎባላይዜሽን ስርአት ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታና ፍጥነት የምርት እድገትን እያስገኘ ነው። ግን ይህ እድገት ተብየ ነገር እዚህም ላይ ከልማት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። እንዲያውም ተጻራሪ ነው። ባለፈው ታህሳስ ወር የቀድሞው የአሜሪካን ፕሬዜዳንት ቢል ክሊንተን ከቢቢሲ ጋር ባደረጉት ውይይት ላይ ግሎባላይዜሽን ያመጣውን እድገት በአድናቆት ከዘረዘሩ በኋላ ስለሁኔታው አደገኛነት ሲናገሩ ይህ የግሎባላይዜሽን ሂደት ከአለም ህዝብ በትንሹ አንድ ሶስተኛውን ማለትም ሁለት ቢልየን ህዝብ ወደ ጎን ትቶ የሚከንፍ ሂደት ነው ሲሉ ተናግረዋል። የቀድሞ የክሊንተን የኢኮኖሚ አማካሪ፣ የቀድሞ የአለም ባንክ ምክትል ፕሬዜዳንትና በአለፈው አመት በኢኮኖሚክስ የኖቤል ሽልማት ያገኙት ጆሴፍ ስቲግሊዝ በቅርቡ ባወጡት አንድ መጽሃፍ ሁኔታውን ሲያጠቃልሉ

«ዛሬ ግሎባላይዜሽን አይሰራም። ለአለም ድሆች አይሰራም። ላካባቢ ጥበቃ አይሰራም። ለአለም ኢኮኖሚ መረጋጋት አይሰራም» በማለት ጽፈዋል።

በግሎባላይዜሽን ስለተገኘው የማይናቅ እድገት ምንነት ባለፈው አመት የተባበሩት መንግስታት የንግድ፣ የኢንዱስትሪና የልማት ኮሚሽን ይፋ ባደረገው ዘገባ ባለፉት አስር አመታት የሆነውን ሲያጠቃልል ከአለም ህዝብ የሃያ ከመቶው ገቢ ጨምሩዋል አምሳ ከመቶው ደግሞ ከዛሬ አስር አመት ዛሬ ደህይቷል በማለት አስታውቋል። የቀረው ሰላሳ ከመቶው ባለበት በመርገጥ ላይ ያለ ህዝብ መሆኑ ነው።

እንዲያውም እንጨምርበት። እድገት ሌላ ልማት ሌላ ማለት ብቻም አይበቃም። ሁለቱ ከፉኛ ተጻራሪ ሊሆኑ ይችላሉ። ጥቂቶች እድገታቸውን ሲያሳድዱ የብዙሃን የልማት በር ተጠርቅሞ ሊዘጋ የሚችልበት ሁኔታ አለ።

የዚህ ክፉኛ የተዛባ ሁኔታ የመጀመሪያው ጠንቅ ድህነት በገፍ ሲፈለፈል የግድ አለ መረጋጋት ይከተላል። አንደኛ ለጥቂቶች ጥቅም የሚሰራው የኢኮኖሚ ስርአት ከአመት አመት በገፍ የሚፈለፍላቸውን ድሆች ለመቋቋም አፋኝ የፖለቲካ ስርአት መትከሉ የግ ድ ይሆናል። በኛ አገር «አብዮታዊ ዴሞክራሲ» የሚባለው ፈሊጥ ነው። ሁለተኛ ድህነ ትና አፈና እየከፉ ሲሄዱ ደግሞ የግድ አመጽንና አለመረጋጋትን ያስከትላሉ። ሶስተኛው ችግር ዛሬ በአፍሪካ እንደምናየው እነዚህ በመሰረቱ በግፈኛው የውስጥና አለም አቀፉ የ ኢኮኖሚ ስርአት የሚፈለፈሉ ግጭቶች ግልጽ በሆኑ አማራጮች ዙሪያ የሚካሄዱ ትግሎ ች አይደሉም። «እህያውን ፈርቶ ዳውላውን» እንዲሉ ይህንን ስርአት ጨርሰው «ረስተ ው» በአንድ በኩል በአለም አቀፍ ደረጃ ማፍያውም፣ የአልማዝና የሌላ ማእድንና የመ ሳሪያ ኮንትሮባንዲስቱም፣ ቅጥረኛ ወታደሩም ገብቶ የሚፈተፍትባቸው በውስጥ ደግሞ የ ብሄርና የሃይማኖት ገጽታ እየያዙ የሚካሄዱ «እጅ አግር» የሌላቸው ትርምሶች ናቸው። በዚህ ሁኔታ እድገት የሚሉት ፈሊጥ የህዝቦችን የመልማት እድል እየዘጋ እንደሆነ ግል ጽ ነው።

ሁለተኛ ጠንቅም አለ። ከፍ ብለን የጠቀስናቸው የቀድሞ የአለም ባንክ ምክትል ሊ ቀመንበር የጠቆሙት የአካባቢ ውድመት ጉዳይም አለ። መጀመሪያ ነገር ጥቂቶች ለጥቂ ቶች የሚያሳድዱት እድገት ተብየ ነገር በተቻለ ፍጥነት የተቻለውን ያህል ማምረትና ማ ትረፍ በሚል ህዝብንም፣ መሬትንም፣ አካባቢንም በሚዝቅና በሚዘርፍ «ለነገ» በማይል ስግብግብ ፍልስፍና ላይ የተመረኮዘ አካሄድ ነው። የነጻ ተብየ ገበያው ግርግርና እጅ አ ግር የሌላቸው ትርምሶች በሚያዋክቡት ህብረተሰብ ውስጥ በሃገር ውስጥም ሆነ በአለም አቀፍ ደረጃ ለመጭው ትውልድ ቀርቶ ለነገ ማለት የማይችሉ ሃይሎች እድገታቸውን ሲያሳድዱ ስለ አካባቢ ውድመት የሚጨነቅ እምብዛም ሃይል አይኖርም። በአለፉት ስድ ስት ወራት እንኳን በዚህ ጉዳይ በሃገራችን እየደረሰ ስላለው ጥፋት ከተባበሩት መንግስታ ት የተለያዩ አገልግሎቶችና ከሌሎች ኢንቫየርሜንታሊስቶች የተሰጡ ዘገባዎችን ብንመለ ከት በዚህም በኩል ኢትዮጵያችን ወደ ጥፋት እየሄደች መሆኗን መገንዘብ እንችላለን። ይህ የአካባቢ ውድመት ዝም ብሎ እስከቀጠለ ድረስ ደግሞ ነገ «ዘንቦ ተባርቆ» አገራች ን ነጻ ወጥታ፣ ዴሞክራሲ ሰፍኖ ህዝባችንን የልማት ጎዳና እናስይዛለን የምንል ከሆነ ለ «ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ» አይነት አጉል ግርግር እየተመቻቸን እንደሆነ ግልጽ ነው።

በአጭሩ ዛሬ እድገትንና ልማትን በተመለከተ ሁለት ራእዮች ከመቸውም ይበልጥ የሚፋለሙበት ወቅት ውስጥ ነን።

በመጀመሪያ የኛን ራእይ እናስቀምጥ። ለኛ እድገት ማለት በየእለቱ፣ በየአመቱ የህ ዝብን ተጨባጭ ኑሮ ለማሻሻል የሚደረገውን ጥረት እንደ ተቀዳሚ አላማና እንደሞተር አድርጎ የሚንቀሳቀስ ሂደት ነው። እድገት በህዝቡ ተሳትፎ ለህዝቡ ስጋዊና መንፈሳዊ ፍ ላጎቶች መልስ ለመስጠት መንቀሳቀስ ነው ብለን ከተነሳን እድገትና ልማት ተያይዘው የ ሚሄዱበት «በጎ አዙሪት» ወይም «ቨርቸስ ሰርክል» እንፈጥራለን። ይህም ማለት የእድገ ታችን የትኩረት ትኩረት የህዝባችንን የንጹህ ውሃ፣ የምግብ፣ የመጠለያ፣ የመብራት፣ የ ጤና ጣቢያ፣ የትምህርትና የስራ ጥማት ለማርካት የሚደረግ እንቅስቃሴ ላይ መሆን ይኖ ርበታል ማለት ነው። በዚህ ሁኔታ ስንንቀሳቀስ በማያጠራጥር ሁኔታ እድገት ይመጣል። ግን ይህ እድገት ከዛሬው እድገት ተብየ ነገር እንደሰማይና ምድር የተለያየ ነው። ያኔ በ የአመቱ ስለእድገት ስታቲስቲክስ ስንደረድር በአንድ በኩል ኢኮኖሚው ይህንን ያህል አ ድጓል በሌላ በኩል ግን ስራ አጥነትና ድህነት ከአምናው ዘንድሮ ጨምረዋል እያልን ባ ጭሩ አገሪቱ ከብራለች ህዝቡ ግን ደህይቷል እያልን አንወለጋገድም።

ላይ ላዩን ሲታይ ታዲያ ይህንን ማን ይቃወማል? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ሁ ለተኛው ራእይ ይህንን ሂደት የሚቃወም ጸረ ህዝብ ራእይ ነው። እድገትን የህዝብ ፍላጎ ቶችን ከማርካት አንጻር ሳይሆን ከገበያና ከህዝብ የመግዛት ችሎታ አቀራኝቶ የሚያይ ራእይ ነው። ችግሩ በድሃ አገር ውስጥ የሚኖር ህዝብ ድሃ ነው። ከመግዛት ችሎታ አን ጻር ሲታይ ወራጅም ተሳፋሪም የሌለበት አውቶቡስ ነጅው ዝምብሎ የሚያልፈው «ደረ ቅ ጣቢያ» የሚባለው አይነት መሆኑ ነው። ጸረ ህዝቡ «የእድገት» ራእይ ለውሃው፣ ለ

መጠለያው፣ ለምግቡ፣ ለመብራቱ፣ ለትምህርቱን ለጤና አገልግሎቱ መክፈል ለማይችል ህዝብ መስራትን እንደትርፍ ድካም ይቆጠራል። እንደ ኢትዮጵያ ባሉ «ድሃ» በሚባሉ አገሮች ሃብቱ፣ ገንዘቡ፣ ገበያው ያለው ውጭ ነው። ስለዚህ የኢኮኖሚው እድገት ውጭ ገበያ ላይ ማተኮር ያስፈልገዋል። ባይሆን ነገ ተነገ ወዲያ በዚህ አቅም ላለው ስናመርት በሚገኘው እድገትና የውጭ ምንዛሪ ሃገሪቱ ስትከብር ፊታችንን ወደ ህዝብ እናዞራለን የሚል ስትራቴጂ አለ። ከዚህ በፊት እንደተጠቆመው ይህ «ሁሉ ነገር ወደ ውጭ ገበያ» ለማለት የሚቃጣው ስትራቴጂ ማንም የበለጸገ አገር ያልተከተለው አፍሪካን ግን ከባሪያ ፍንገላ ጊዜ ጀምሮ ለብዝበዛ፣ ለድቀት፣ ለክስመት የዳረጋት አካሄድ ነው። የግሎባላይዜሽን አራማጆች የሚመክሩንና በነአለም ባንክና የአለም የገንዘብ ድርጅት አማካኝነት ሊጭኑብን የሚፈልጉት በዚሁ ላለፈው አምስት መቶ አመት ባልሰራ አሁንም ሊሰራ በማይችል የጥፋት ጎዳና እንድንቀጥል ነው። በኢትዮጵያ ደረጃ የወያኔ መሪዎች የኢኮኖሚ ፖሊሲ፣ በአፍሪካ ደረጃ ደግሞ ኔፓድ የተባለው አዲስ የልማት ስትራቴጂ አገራችንንም አህጉራችንንም ወደ ጥፋት ይዘው በመንጎድ ላይ ያሉት ለዚህ ስትራቴጂ ተንበርክከው ለበለጸጉት እንጂ ለኛ ባልተበጀና ለኛ በማይሰራ የአለም አቀፍ የኢኮኖሚ ስርአት ውስጥ ዘው ብለው ለመግባት ፈቃደኞች በመሆናቸው ነው።

ይህ እስከሆን ድረስ ደግሞ ከአመት አመት ተመድም ሆነ ሌሎች ተቋሞች አሁን በተያዘው መልክ «ኢኮኖሚው በያዝነው አመት ይህንን ያህል ከመቶ እድገት አሳይቷል ህዝቡ ደግሞ በዚሁ በያዝነው አመት ካለፈው በዚህ ያህል ደህይቷል» እያሉ መቀጠላቸው አይቀሬ ነው። ይህ እንዳይሆን ከተፈለገ «እድገት ማለት ልማት ማለት ነው» የሚሉ ህዝባዊ ሃይሎች በሃገር ውስጥ በእድገትና በነጻ ገበያ ስም እየተፈጸመ ያለውን ግፍና አደገኛ ሂደት ለመቃወም ግልጽ አማራጭ ይዘው መነሳት ይኖርባቸዋል። በአለም አቀፍ ደረጃም ቢሆን «ወደድንም ጠላንም ግሎባላይዜሽንን መቃወም አንችልም» ከሚል ተንበርካኪ አቋም በመነሳት ገብተን እንዳክርበት የሚሉ ሃይሎችን መቃወም አለብን። ይህ ማለት ግን «ግሎባላይዜሽንን» በጭፍን መቃወም ማለት አይደለም። ዛሬ በአምስቱም አህጉራት «ሌላ አይነት ግሎባላይዜሽን» በሚል አላማ አለም አቀፋዊ የሆነ እንቅስቃሴ እየተነሳሳ ነው። እኛም ከዚህ ተደባልቀን ለሃገራችንና ለህዝባችን ህልውና መዋደቅ ይኖርብናል። ያኔ እድገትና ልማት እርስበርስ መጣፋት ሳይሆን ተያይዘው የሚራመዱበት ሁኔታ እንፈጥራለን።